# የአራት ኪሎ ቁልፍ የት ነው?

ኢብሳ ነመራ 02-28-18

*ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ስዩመ እግዜአብሄር ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ።* ይህ በ1967 ዓ/ም የተወገዱት የመጨረሻው የዘውዳዊ ስርአት ንጉሰ ነገስት መጠሪያ ነው። የንጉሰ ነገስቱ መጠሪያ ላይ እንደተገለጸው የስልጣናቸው ምንጭ መለኮታዊ ነው። በምድራዊ ጥበብ የማይመረመር፣ በምድር ላይ ሊጠየቅ የማይችል፣ ከሰማይ የተሰጠ ምሉዕ ስልጣን ነው። ይህ የነገስታቱ ስልጣን ፍጹም ነው። ነገስታቱ የህገመንግስትና የህጎች ሁሉ ምንጭ ናቸው። ህዝብ በነገስታቱን ጥቅምና ፍላጎት መሰረት ከመገዛት ያለፈ የራሱ መብቶችና ነጻነቶች፤ ጥቅሞችና ፍላጎቶች እንዳሉት አይቆጠርም። የሃገሪቱ ሃብት በሙሉ የንጉሱ ነው፤ የሃገሪቱ መሬት ላይ የማዘዝ ስልጣን ያለው ንጉሱ ነው። ለፈለገው ይለግሳል፤ ላልፈለገው ይነሳል። እናም በኢትዮጵያ የነበረው የዚህ አይነት ንጉሳዊ ፈላጭ ቆራጭ (absolute monarchy) ስርአት ነበር።

ይህ ዘውዳዊ ስርአት ከ43 ዓመታት በፊት በህዝባዊ ትግል ተወግዷል። ከዘውዳዊው ስርአት መወገድ በኋላም ቢሆን ስልጣን የኢትዮጵያ ህዝብ እጅ አልገባም። ዘውዳዊውን ስርአት ያስወገደው ትግል የተደራጀ ስላልነበረ፣ በወቅቱ የተደራጀና የታጠቀ ብቸኛ ሃይል የነበረው ወታደራዊው ክፍል ስልጣኑን ጠልፎ እጁ አስገባ። ወደስልጣን የመጡት ቁጥራቸው በመቶዎች የሚቀጠሩ ከፍተኛና የመስመር መኮንኖች እንዲሁም ጥቂት የበታች ሹማምንት ነበሩ።

እነዚህ በመቶዎች የሚቆጠሩ ወታደሮች ራሳቸውን *ወታደራዊ ደርግ* ወይም *ወታደራዊ ምክር ቤት* በሚል ስያሜ አደራጅተው ስልጣን ላይ ወጡ። ወደስልጣን የመጡት ህዝብ መንግስት እስኪመሰርት በጊዜያዊነት ሃገር ለማስተዳደር ብለው ነበር። ይሁን እንጂ ስልጣናቸውን ለህዝብ ማስረከብ አልፈቀዱም። ከጊዜያዊው ወታደራዊ መንግስት ራሱን ወደቋሚነት ቀየረ። ወደዚህ ቋሚ መንግስትነት ለመሸጋገር የኢትዮጵያ ሰራተኞች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን (ኢሰፓአኮ)፣ ኢሰፓአኮ ወለደው የተባለ የኢትዮጵያ ሰራተኞች ፓርቲ (ኢሰፓ)፤ በመጨረሻ ኢሰፓ የመሰረተው የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢህዲሪ) መንግስት ውስጥ አልፏል። በዚህ ሂደት ውስጥ እነዛው የመጀመሪያዎቹ ወታደሮች ናቸው ገዢዎች የነበሩት።

የእነዚህ ወታደራዊ ገዢዎች የስልጣን ምንጭ ብረት ነው፤ የታጠቁት ጠመንጃ። እርግጥ ይህን ከጠመንጃ የመነጨ ስልጣናቸውን ኮምኒስታዊ ርዕዮተ ዓለም ቀብተውታል። ወታደራዊ ቡድኑ የህገመንግስትም የህግም ምንጭ ነው። ውሳኔው ፍጹም፣ የማያስጠይቅ ነው። በዚህ ቡድን አተያይ ህዝብ በተፈለገ መንገድ የሚነዳ ተገዢ እንጂ የራሱ እድል ላይ የመወሰን መብትና ነጻነት ያለው አካል አይደለም። ስርአቱ የቡድን ፈላጭ ቆራጭ (absolute oligarchy) ነበረ።

አሁን ሁለቱም ስርአቶች ታሪክ ሆነው ቀርተዋል። አሁን ህገመንግስታዊ ስርአት ላይ እንገኛለን፤ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስታዊ ስርአት። ህገመንግስቱ የህዝቡ ነው። ህገመንግስቱ ህዝብ *በዚህ አኳኋን መተዳደር እፈልጋለሁ* ብሎ የቀረጸው የህጎች ሁሉ ህግ የሆነ ሰነድ ነው። መንግስት ሃገሪቱን በህገመንግስቱ መሰረት ለማስተዳደር በውክልና የሚሰየም፣ ህገመንግስቱን ተግባራዊ ማድረግ ካልቻለ በማንኛውም ስርአት ሊነሳ የሚችል፣ ስልጣኑ ህገመንግስቱ ላይ ህዝብን ለማገልገል ተከርክሞ በተሰጠው አቅም የተገደበ አካል ነው። በቸኛ የመንግስት የስልጣን ባለቤትና ምንጭ ህዝብ ነው።

ህዝብ ብቸኛ የስልጣን ባለቤትና ምንጭነት የሚገልጸው በምርጫ ከተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ግለሰቦች መሃከል *መብትና ነጻነቴን፤ ጥቅምና ፈላጎቴን ያስጠብቅልኛል* ብሎ ላመነበት ድምጹን በሚሰጥበትና አብላጫ ድምጽ ያገኘው ውክልና በሚወስድበት የዴሞክራሲ ስርአት ነው። በኢትዮጵያ ከዚህ ውጭ ስልጣን ማግኘት አይቻለም። ከዚህ በተጨማሪ ሃገሪቱ የምትተዳደረው ራሳቸውን በራሳቸው በሚያስተዳድሩ ክልሎች በተዋቀረ ፌደራላዊ ስርአት ነው። የፌደራል መንግስቱ ስልጣን የመነጨው የሃገሪቱ የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤት የሆኑት ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው ከሚያስተዳደሩባቸው ክልላዊ መንግስታት ነው። የፌደራል መንግስቱ ስልጣን ከክሎች ላይ ተቀንጭቦ የተሰጠ ነው።

በዚህ መሰረት ማንኛውም አካል ወደመንግስት ስልጣን ለመምጣት በአሳታፊ፣ ፍትሃዊ፣ ነጻና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ በአብላጫ ድምጽ ብቸኛ የስልጣን ባለቤትና ምንጭ የሆነውን ህዝብ ውክልና ማግኘት ይኖርበታል። አሁን በኢትዮጵያ ስልጣን በመለኮታዊ ሃይልና በፍጹም ርዕዮተ ዓለም ሽፋን በርስትነት የሚያዘባት ሃገር አይደለችም። ስልጣን በህዝብ ውክልና የሚገኝ ማገልገያ መሳሪያ ነው። ሃገሪቱ ባለፉት ሁለት ተኩል አስርት ዓመታት በዚህ ውስጥ አልፋለች። አሁን የህዝብ የስልጣን ብቸኛ ባለቤትነትና ምንጭነት የሚረጋገጠበት የምርጫ ስርአት በህግ የተደነገገ ብቻ ሳይሆን ባህልም እየሆነ ነው።

አሁን ህዝብ ማንኛውም አካል ከምርጫ ውጭ ወደስልጣን እንዲመጣ የሚፈቅድበት ሁኔታ የለም። ይህን ስል ከምርጫ አፈፃፀም ጋር ተያይዞ ምንም ያጋጠመ ችግር የለም እያልኩ አለመሆኑ እንዲታወቅልኝ እፈልጋለሁ። ህዝብ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችና መንግስት ከዴሞክራሲ ጋር ያላቸው ትውውቅ ባለመጎልበቱ የተፈጠሩ የአፈጻጸም ችግሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይገመታል። እነዚህ ስህተቶች ግን ሊሻሻሉ እንደሚገባቸው ችግሮች መወሰድ ያለባቸው መሆኑ እንደተጠበቀ፣ ባለፉት ምርጫዎች በክልልና በፌደራል መንግስት የተገኘውን ስልጣን ሊቀይሩ የሚችሉ አልነበሩም።

እንግዲህ፤ በኢትዮጵያ ባለፉ ሁለት ተኩል አስርት ዓመታት አምስት ሃገራዊ ምርጫዎች ተካሂደዋል። በእነዚህ ምርጫዎች በህገመንግስቱ መሰረት ትልቁ የስልጣን አካል የሆነው የኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ተመርጠው መንግስት እያደራጁ ሃገሪቱን ሲያስተዳድሩ ቆይተዋል። የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት የሚመረጡት፣ በህገመንግስቱ አንቀጽ 54 “የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት” በሚል ርእስ ስር፣ በንኡስ አንቀጽ 1 ላይ *የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ ሁሉ አቀፍ፣ ነጻ፣ ቀጥተኛ፣ ትክክለኛ በሆነና ድምጽ በሚስጥር በሚሰጥበት ስርአት በየአምስት አመቱ ይመረጣሉ* በሚለው ድንጋጌ መሰረት ነው።

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የህግ አውጭ አካል ነው። ህግ ያወጣል፣ ህገመንግስቱና ከህገመንግስቱ የመነጩ ሌሎች ህጎች፣ ፖሊሲዎችና ደንቦች በአስፈጻሚውን አካል - በጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በሚንስትሮች ምክር ቤትና የምክር ቤቱ አባላት በሆኑ የተለያዩ ሚኒስትሮች በአግባቡ መፈጸማቸውን የመቆጣጠር ስልጣን አለው። አስፈጻሚው አካል ተጠሪነቱ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው።

አስፈጻሚው አካል የሚሰየመውም በምክር ቤቱ ነው። ከፍተኛ የአስፈጻሚነት ስልጣን የተሰጠው ጠቅላይ ሚኒስትሩ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 73 “የጠቅላይ ሚኒስትሩ አሰያየም” በሚለው ርእስ ስር በንኡስ አንቀጽ 1 *ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት መሃከል ይመረጣል* በሚል በተደነገገው መሰረት ይመረጣል። ለጠቅላይ ሚኒስትርነት የሚወዳደረውን እጩዎች የሚያቀርበው በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አብላጫ ድምጽ አግኝቶ መንግስት የመሰረተው ፓርቲ ነው። በህዝብ ውክልና መንግስት የመሰረተው ፓርቲ የሚያቀርባቸው እጩዎች ላይ ምክር ቤቱ ድምጽ በመስጠት አብላጫ ያገኘው ጠቅላይ ሚኒስትር ይሆናል። ከዚህ የህዝብ የውክልና ተሳተፎ ከሚረጋገጥበት መንገድ ውጭ ጠቅላይ ሚኒስትር መምረጥ የሚያስችል መንገድ የለም።

በዚህ ሂደት የተመረጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማርያም ደሳለኝ ሰሞኑን ስልጣናቸውን ለመልቀቅ ለሰየማቸው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥያቄ ማቅረባቸው ይታወቃል። በመንፈቅ እረፍት ላይ የሚገኘው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወደስራ ሲመለስ ጥያቄያቸውን ይቀበላል ተብሎ ይጠበቃል። በምትካቸውም ሌላ ጠቅላይ ሚኒስትር ይሰይማል። አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር የሚሰየመው በምክር ቤቱ ውስጥ አብላጫ ድምጽ አግኝቶ መንግስት በመሰረተው ገዢው ፓርቲ አቅራቢነት ነው። ገዢው ፓርቲ ከምክር ቤቱ አባላት መሃከል ለጠቅላይ ሚኒስትርነት ሃላፊነት ይመጥናል ያለውን ወይም ያላቸውን እጩዎች አቅርቦ ምክር ቤቱ ድምጽ እንዲሰጥ ያደርጋል። አብላጫ ድምጽ ያገኘው ጠቅላይ ሚኒስትር ይሆናል። ከቀናት በኋላ በዚህ መሰረት አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር ይመረጣል ተብሎ ይጠበቃል።

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የህዝብን የስልጣን ምንጭነትና ባለቤትነት ከሚያረጋግጠው በምርጫ የሚሰጥ የህዝብ ውክልና ውጭ ወደስልጣን መምጣት የሚያስችል አንዳችም ህገመንግስታዊ መንገድ የለም። አራት ኪሎ የሚገኘው የፌደራል መንግስቱ ትልቁ የስልጣን  አካል የሆነው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትና ትልቁ አስፈጻሚ አካል የሆነውን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት የሚመራው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣናቸው ከህዝብ የመነጨ ነው። የራሱ የፌደራል መንግስቱ ስልጣን የመነጨው ደግሞ የህገመንግስቱ ባለቤትና የኢትዮጵያ የሉአላዊ ስልጣን ባለቤት የሆኑ የኢትዮያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው ከሚያስተዳደሩባቸው ክልላዊ መንግስታት ነው።

አንድ አካል ከህዝብ ውክልና ውጭ 'ሆ' ብሎ ምክር ቤት መግባት ካለመቻሉም ባሻገር፣ በሆነ ሊገመት የማይችል አጋጣሚ 'ሆ' ብሎ መግባት እንኳን ቢችል፣ የፌደራል መንግስቱ ስልጣን ምንጭ የሆኑት ክልላዊ መንግስታት ስለማይቀበሉት ምናልባት ለሰአታት ወንበር ላይ ከመቀመጥ ያለፈ ሃገሪቱን መምራት አይችልም። የአራት ኪሎ ቁልፍ ያለው ህዝብ፤ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች እጅ ነው። ይህ ቁልፍ ከምርጫ ኮሮጆ ውጭ ከየትም ሊገኝ አይችልም።